አጥቢያ ዶት ኮም

ቴክኖሎጂ ለቤተክርቲያን

# ስልጠና፡- ሥራ አመራር 5 - ውጤታማ እቅድ፣ ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ

©አጥቢያ ዶት ኮም

1. መግቢያ
    - ውይይት
        - እቅድ ሲባል በአእምሮአችሁ የሚመጡ ነገሮችን ግለጹ
        - እቅድ አስፈላጊ ነውን ? ለምን ?
        - እቅድ አለን? ካለን እቅዱን እንመራበታለን?
    - የእቅድ ምንንት
        - የሚፈለገውን ውጤት ለማስመዝገብ የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት ነው
        - የአመራር ዋና መሳሪያ ነው
    - መንፈሳዊ እቅድ
        - ፈቃደ እግዚአብሔርን ታሳቢ ያደረገ - "ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል" ያዕ 4፣ 15
        - ተግዳሮቶቹ ከአለማዊ እቅድ ለየት ይላሉ - "መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።" ኤፌ 6፣ 12
2. የውጤታማ እቅድ መገለጫዎች
    - ተዋረዳዊ
        - ከመዋቅር አንጻር ፡ የዋና ክፍል => የንዑስ ክፍል => ኮሚቴ / የግብረ ኃይል
        - ከጊዜ አንጻር ስልታዊ: መሪ እቅድ => አመታዊ => የሩብ አመት => የወር => የሳምንት
    - አሳታፊነት: ተግባሪዎችን፣ ባለድርሻ አካላትን
    - ግብ /ውጤት ተኮር
        - ምን እንስራ ሳይሆን ምን ውጤት እናምጣ በሚል እሳቤ ማቀድ
        - ግብ እና ተጨባጭ ውጤትን ታሳቢ ያደረገ /OKR/
        - ግልጽ፣ ተለኪ፣ ተተግባሪ፣ ፋይዳ ያለው፣ በጊዜ የተገደበ /SMART/
    - ተደራሽ
        - የተጠናቀረ እና የተሰነደ
        - በቅርብ / በቀላሉ መገኘት የሚችል
        - የተለያዩ የመረዳት አቅሞችን ታሳቢ ያደረገ
        - የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ታሳቢ ያደረገ

3. የውጢታማ እቅድ አዘገጃጀት
    - 5ቱ የግብአት አርእስት
        1. ገዥ/የበላይ ሰነዶች እና ገዥ/የበላይ እቅዶች - ቃለ አዋዲ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የአሰራር መመሪያ፣ ፖሊሲዎች፣ ስልታዊ ዕቅድ/መሪ ዕቅድ፣ የበላይ አካላት ዕቅድ ....
        2. ያለፉ ተሞክሮዎች - ያለፉ ስኬት እና ተግዳሮቶች፣ ያለፉ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ...
        3. አሁናዊ ቁመና - የሰው ኃይል ብዛት እና የብቃት ደረጃ፣ በጀት፣ ልዩ ልዩ ጥናቶች፣ የተመዘገቡ ክስተቶች ...
        4. ኩነቶች - በዓላት፣ የታቀዱ መርሐግብሮች ...
        5. የተጓዳኝ አካላት ግብአት - የጋራ ስራዎች፣ ተመጋጋቢ ስራዎች፣ አቅም ...
    - እንዴት እናቅድ ?
        1. ግብአት ዝግጅት
        2. መነሻ እቅድ /ግብ እና የሚጠበቅ ውጤት
        3. በውይይት ማጎልበት
        4. ዝርዝር እቅድ /ተፈጻሚዎች
4. የአፈጻጸም ክትትል
    - ለምን ?
        - በጊዜ ማስተካከያን ለማድረግ
        - ኃላፊነት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን
        - ጠቃሚ ልኬቶችን ለመከታተል
        - ተደጋጋሚ ጉዳዮችን /Patterns ለማጤን
    - እንዴት ?
        - ስለ አላማው አወንታዊ አረዳድ መፍጠር
        - እቅዶች ተለኪ እንዲሆኑ በማድረግ
        - ሥርዓት መዘርጋት
            - የሪፖርት
            - የመረጃ አሰባሰብ
            - የመረጃ ተንተና
5. ተግባራዊ እንቅስቃሴ
    - በእቅድ ዙሪያ የተቀመጡ መነሻ ቅጾችን ይመልከቱ - https://atbiya.com/a/templates
    - አሁን ያለውን የእቅድ ባህል/ሥርዓት ይገምግሙ

**ለተጨማሪ ንባብ**

- https://en.wikipedia.org/wiki/SMART_criteria
- https://en.wikipedia.org/wiki/Objectives_and_key_results